# የአጼ ገላውዴውስ የሐይማኖት ውሳኔ

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ፣ ሃይማኖቴና የእስራኤላውያን ነገሥታት ሃይማኖት፣ በመንግሥቴም ግዛት ውስጥ የሚገኙ ምእመናን የመንጋዬ ሃይማኖት ይህ ነው።

1) እኛ በአንድ አምላክ እናምናለን።

2) በአንድ ልጁም በኢየሲስ ክርስቶስ እናምናለን። ይኸውም ቃሉ፣ ኃይሉ፣ ምክሩ፣ ጥበቡ ነው። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር የነበረ ነው። በኋለኛውም ዘመን ከመለኮታዊ ምግባሩ ሳይለይ ወደ እኛ መጣ። ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ። በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ፣ ፍጹም ምሉዕ ሰው ሆነ። በጰንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በዕንጨት ላይ ተሰቀለ፣ ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሦስተኛውም ዕለት ተነሣ። ከዚህ በኋላ በአርባ ቀን በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፣ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድ በክብር ይመጣል፣ ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም።

3) ከአብ በሠረጸ፣ ጌታ፣ አዳኝ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን።

4) ኀጢአትን ለማስተሰረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

5) ለዘለአለም ሕይወት የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፣ አሜን።
እኛስ እውነተኛ በሆነው በጥርጊያውና በነጉሥ መንገድ እንሄዳለን፣ ከአባቶቻችን ትምህርት ወደ ግራም ወደ ቀኝም አናዘነብልም። ዐስራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ፣ ሰባ ሁለቱ አርድእት፣ በንቅያ የተሰበሰቡ ሃይማኖታቸው የቀና ሶስት መቶ አስራ ስምንቱ፣ በቊስጥንጥንያ የተሰበሰቡ አንድ መቶ ሃምሳው፣ በኤፌሶን የተሰበሰቡ ሁለት መቶው።

የናዖድ ልጅ፣ የወናግ ሰገድ ልጅ፣ በመንግሥቴ አጽናፍ ሰገድ የምባል፣ የኢትዮጵያ ንጉሥ እኔ ገላውዴዎስ፣ እንዲህ እሰብካለሁ፣ እንዲህም አስተምራለሁ።

6) ሰንበትን የምናከብራት ምክንያት፣ “ደሙ በልጆቻችን ላይ ይሁንብን” (ማቴ 27፥25) ብለው ክርስቶስን እንደሰቀሉት እንደ አይሁድ ሰንበት አይደለም። እነዚህ አይሁድ ውሃ አይቀዱም፣ እሳት አያነዱም፣ ወጥ አይሠሩም፣ እንጀራ አይጋግሩም፣ ከቤት ወደ ቤት አይሄዱም። እኛ ግን የምናከብራት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንዳዘዙ ቅዳሴን በመቀደስና ግብር ማዕድ በመሥራት ነው እንጂ እንደ አይሁድ ሰንበት አይደለም፣ ይህችውም ዐዲሲቱ ዕለት ናት። “እግዚአብሔር የሠራት ዕለት ይህች ናት፣ እንደሰትባት፣ ሐሤትም እናድርግባት።” ብሎ ዳዊት ስለርሷ ተናገረ፣ (መዝ 117(118)፥24)። በዚች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና፣ በዚች ዕለት መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን ለሐዋርያት ወርዶአልና፣ በዚች ዕለት ሁልጊዜ ድንግል በሆነች በቅድስት ማርያም ማሕፀን ሰው ሆኖአል፣ በዚች ዕለት ለጻድቃን ሽልማት ለመስጠት፣ ኃጥአንን ለመቅጣት ዳግመኛ ይመጣል።

7) ሰለ ሥርዐት ግዝረትም እንደ አይሁድ የምንገዘር አይደለንም፣ የጥበብ ምንጭ የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና፣ “መገዘር አይጠቅምም፣ አለመገዘርም ግዳጅ አይፈጽምም፣ ዐዲስ ፍጥረት ነው እንጂ፣ ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው።” (ገላ. 5፥6፣ 6፥15) ዳግመኛም ለቆሮንጦስ ሰዎች “የተገዘረ ቊልፈትን (አለመገዘርን) አይሻ።” (1 ቆሮ 7፥18)። የጳውሎስ የትምህርቱ መጽሐፍ ሁሉ በኛ ዘንድ አለ። ስለ ግዝረትና ስለ ቊልፈት ያስተምረናል። ነገር ግን በኛ ዘንድ ያለው ግዝረት፣ እንደ ኢትዮጵያና እንደ ሮባ የፊት መተልተል፣ እንደ ሕንድ ሰዎች የጆሮ መነደል ያለ የአገር ልማድ ነው። ይህን የምናደርገው በኦሪት ሕግ አይደለም፣ በሰው ልማድ ነው እንጂ።

8) ዐሳማንም ስለመብላት፤ ከመብላት የተከለከልነው፤ እንደ አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም። የሚበላውን አንጸየፈውም፤ አናረክሰውም፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም። አባታችን ጳውሎስ ለሮም እንደ ጻፈው "የሚበላ የማይበላን አይንቀፈው (አይናቀውም)፤ እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና። እግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም። ለኑጹሓን ሁሉ ንጹሕ ነው። ለሰው ክፉው፤ ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው።" (ሮሜ 14፡3፤ 17፣ ቲቶ 1፡15፤ 1ቆሮ 8፡9-13)። ወንጌላዊ ማቴዎስም "ከአፍ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም፤ ወደ ሆድ የሚገባው ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል፤ ይፈሳል፤ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል።" አለ፤ (ማቴ 15፡11, 17፤ ማር 7፡15)። ይህ አባባሉ ከኦሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስህተት ሕንጻ ሁሉ አፈረሰው። እኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ፤ በትእዛዜ የሚያስተምሩ ዐዋቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው። ከወንጌል መንገድ፤ ከጳውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም። በኛም የታሪክ መጽሐፋችን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት የዐሳማ ሥጋ እንዲያበሏቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ።

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ እንዳለው የእንስሳትን ሥጋ ከመብላት ይወሰናል። የዓሳ ሥጋ የሚወድ አለ፤ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድ አለ፤ የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ። ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል። የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደዚሁ ነው። ስለ እንስሳት ሥጋ መብል በዐዲሲቱ መጽሐፍ (በዐዲስ ኪዳን) ቀኖናም ሥርዐትም የለም። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው። ጳውሎስም "የሚያምን ሁሉን ይብላ።" አለ፤ (ሮሜ 14፡22-23)።

የሃይማኖቴን እውነት ይታወቅ ዘንድ ይህን ለመጻፍ ተጋሁ። ዳሞት በሚባል ሀገር በሠኔ 23 ቀን 1555 ዓ.ም ተጻፈ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ ከአባ ጎርጎርዮስ ፣ 1972 ፣ ገጽ 178-183

## በግእዝ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ፤ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥት እስራኤላውያን፤ ወሃይማኖተ መርዔትየ እለ ሀለዉ በዐጸደ መንግሥትየ።

1) ንሕነ ነአምን በአሐዱ አምላክ።

2) ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ ቃሉ ወውእቱ ኀይሉ ውእቱ ምክሩ ወውእቱ ጥበቡ ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። ወበደኀሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየዐርቅ እመንበረ መለኮቱ። ወተሰብአ በመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል፥ ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በሠላሳ ክረምት፥ ወኮነ ብእሴ ፍጹመ፥ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፥ ሐመ፥ ወሞተ፥ ወተቀብረ፥ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት፥ ወእምዝ በአርብዓ ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፥ ወነበረ በየማነ አቡሁ፥ ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ፥ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።

3) ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረጸ እምአብ።

4) ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኀጢአት።

5) ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ለሕይወት ዘይመጽእ ለዓለም አሜን።
ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዩሕ አማናዊ፥ ወኢናጸንን ኢለየማን ወኢለጸጋም እምትምህርተ አበዊነ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት፥ ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ፥ ወሰብዓ ወክልኤቱ አርድዕት፥ ወሠለስቱ ምእት ዐሠርቱ ወሰመንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ዘተጋብኡ

በኒቅያ፥ ወምእት ወ፡ነምሳ በቍስጥንጥንያ፥ ወክልኤቱ ምእት በኤፌሶን። ከመዝ እሰብክ ወከመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ፥ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ።

6) ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት፥ አኮ ዘናከብራ ከመ አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ፥ እስመ እሙንቱሰ አይሁድ ኢይቀድሑ ማየ፥ ወኢያነድዱ እሳተ፥ ወኢያበስሉ ጸብሐ፥ ወኢየ፡ኀብዙ ኅብስተ፥ ወኢይትፋለሱ እም ቤት ውስተ ቤት ። ወባሕቱ ንሕነሰ ናከብራ እንዘ ናዓርግ ባቲ ቍርባነ፥ ወንገብር ባቲ ምሳሐ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ። አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ እሑድ፥ እንተ ይእቲ ዕለት ሐዳስ ዘይቤ ዳዊት በእንቲኣሃ "ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር፥ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ፥" እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን፥ ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ፥ ወባቲ ይመጽእ ዳግመ ለዕሴተ ጻድቃን፥ ወለፍዳ ኃጥእን።

7) ወበእንተ ሥርዐተ ግዝረትነ አኮ ዘንትገዘር ከመ አይሁድ፥ እስመ ንሕነ ነአምር ቃለ ምህሮሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘይቤ፥ "ተገዝሮሂ ኢይበቍዕ፥ ወኢተገዝሮሂ ኢያሠልጥ ዘእንበለ ዳእሙ ሐዳስ ፍጥረት፥ ዘውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።" ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ፥ "ዘሂ ነሥአ ግዝረተ ኢይንሣእ ቍልፈተ።" ኵሉ መጽሐፈ ትምህርቱ ለጳውሎስ ሀለወ በ፡ነቤነ፥ ወይሜህረነ በእንተ ግዝረት፥ ወበእንተ ቍልፈት። ወባሕቱ ግዝረትሰ ዘኮነ በ፡ነቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥሐተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወኖባ፥ ወከመ ስቁረተ ዕዝን ዘሰብአ ሕንድ ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በዐቂበ ሕገ ኦሪት፥ ዳእሙ በልማደ ሰብእ።

8) ወበእንተ በሊዐ ሐራውያኒ አኮ ዘንትከላዕ በዐቂበ ሕገገ ኦሪት ከመ አይሁድ፥ ለዘኒ በልዐ ኢናስቄርሮ፥ ወኢናረኵሶ፤ ወለዘኒ ኢበልዐ ከመ ይብላዕ ኢናጌብሮ በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል፥ "ዘኒ በልዐ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ፥ ወለኵሎሙ እግዚአብሔር ተወክፎሙ። መንግሥተ እግዚአብሔር ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ፥ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን፥ ወእኩይሰ ለሰብእ በሊዕ ምስለ ዕቅፍት።" ወማቴዎስ ወንጌላዊ ይቤ፥ "አልቦ ዘይክል አርኵሶቶ ለሰብእ ዘእንበለ ዘይወፅእ እምአፉሁ፥ ወዘሰ ውስተ ከርሥ ይበውእ፥ ወይትገመር ጽመ፥ ወይትገደፍ፥ ወይትከዐው፥ ወያነጽሕ ኵሎ መባልዕተ።" ወብሂለ ዝንቱ ቃል ነሠተ ኵሎ ሕንጻ ስሕተቶሙ ለአይሁድ እለ ተምህሩ እመጽሐፈ ኦሪት።

ሊተሰ ሃይማኖትየ፥ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለ ይሜህሩ በትእዛዝየ በዐጸደ መንግሥትየ፤ ወኢይትገሐሱ እምፍኖተ ወንጌል ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማን፥ ወኢለጸጋም።

ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሎ በመጽሐፈ ዚኣነ፥ እስመ ቄስጠንጢኖስ ንጉሥ አዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለኵሎሙ እለ ተጠምቁ አይሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወባሕቱ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ እንስሳ። ቦ ዘያፈቅር ሥጋ ዓሣ፥ ወቦ ዘያፈቅር በሊዐ ሥጋ ዶርሆ፥ ወቦ ዘይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ በግዕ፥ ወኵሉ በከመ አደሞ ልቡ ይተሉ ከመዝ ውእቱሥምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ በእንተ መብልዐ ሥጋ እንስሳ፤ አልቦ ሕግ፥ ወአልቦ ቀኖና ውስተ መጽሐፍ ሐዳስ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን፥ ወጳውሎስኒ ይቤ "ዘሰ የአምን ኵሎ ለይብላዕ።"

ዘንተ ኵሎ ጽሕቀ ለጽሒፍ ከመ ታእምር ጽድቀ ሃይማኖትየ፥ ተጽሕፈ በዐሠርቱ ወኃምስቱ ምእት በ፡ነምሳ ወ፡ነምስቱ ዓመት እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ዕሥራ ወሠሉሱ ለሠኔ በሀገረ ዳሞት።